# ☆ ዴሞክራሲያ ☆

************************

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን*

************************

## <u>ልዩ እትም</u>

## <u>(የኢሕአፓን 32ኛ የምሥረታ ዓመት በማክበር)</u>

### <u>ዴሞክራሲ ሲሉ ዴሞክራሲ ስንል</u>

በመጋቢት-ሚያዝያ 1964 ዓ.ም ኢሕአፓ የሀገራችን የመጀመሪያው ዘመናዊ የፖለቲካ ፓርቲ-ድርጅት ሆኖ ሲመሠረት፥ የሀገርና የወገን ፍቅርን በድል ተስፋ አጅበው የተነሱት ታጋዮች ለኢትዮጵያ ሕዝባዊና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን በትግላችን እናረጋግጣለን ብለው ፅኑ እምነት ነበራቸው:: ቁጥራቸውና አቅማቸው ማነሱ ከቶም አላሸማቀቃቸውም:: በሕዝብ ድል አድራጊነት ሙሉ ዕምነት ስለነበራቸው፥ ኃያል መስሎና ተሰይሞ የነበረውን የአፄውን ሥርዓት ድል እናደርገዋለን ብለው እርግጠኞች ነበሩ:: ስለ የካቲት አብዮት ድል ትክክል መሆናቸውን ታሪክ ጽፎ አረጋግጦላቸዋል::

ኢሕአፓ በ1964 ዓ.ም ተመሥርቶ እስከ ዛሬም በትግል መስክ ላይ መገኘቱ በራሱ ያለው ታሪካዊ ቦታና አንደምታ ግልፅ ቢሆንም፥ ከዓመት ቆጠራው ባሻገር ደግሞ በዚህ መራራና የትግል ጽናት ሂደት ከድልም ከውድቀትም የተቀሰመውን ተመክሮ በሚገባ ማጤንና ለሚካሄደው ወሳኝ ትግልም አስተዋፅዖ ማድረጉ ይበልጥ ሚዛን አለው:: ያለፈውን በደፈናው እየኮነኑና የታገለውን ትውልድ ቅርስም እያክቸለቸሉ የዛሬና የነገን ትግል ይዘትም ሆነ አቅጣጫ ምን መደረግ አለበት፤ምንስ መደረግ የለበትም ከሚለው ጋር አጣምሮ መረዳት አይቻልም:: “የሰው ጠላቱ ይወጣል ከቤቱ” ነውና፥ የባዕዱን ወረራ ስንታገል ሀገር በቀሉ ሙጃ እየበዛ፥ ሕዝብን ከድል እያገደ ፤ ከቅዱስ ዓላማው እያራቀ፥ አረመኔ ሥርዓትን በማስፈኑ የዴሞክራሲ ሥርዓት ምሥረታ ተልዕኮ፥ እነሆ ከዓመት ዓመት እየተለጋ ዛሬም ትግላችን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለማስፈን ሆኖ ይገኛል:: የጨካኙ ኮለኔል ሥርዓት ትውልድን መትሮና ጨፍጭፎ ሀገርን ሲያሽመደምድ፥ ዘረኛው ወያኔ ደግሞ ሀገርን ራሷን ኢላማ በማድረግ ህልውናዋን ሊሰርዝ--ሊያጠፋ ሲሯሯጥ እነሆ አስራ ሶስት ዓመት ሆነው::

ልጓም ለቅቆ ቼቼ አይበጅምና ያሳለፍነውን ተመክሮ ሳናጤን፥ የዛሬና የነገውን ምን መደረግ አለበት? ትግላችንስ ለምን ግብ ነው? የሚሉትን ጥያቄዎች በአግባብ መመለስ አንችልም:: ዛሬ ጨቋኞቹ ዴሞክራሲ ሲሉና እኛ ዴሞክራሲ ስንል የልዩነቱ ገደል ሰፊ ሆኖ መታየቱ ያለምክንያት አይደለም:: መሬት ለአራሹ፤ መብት ለሰርቶ አደሩ፤ ሕዝባዊ ዴሞክራሲ ለዜጋ፤ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ለጭቁኖቹ፤ ወዘተ ብለን የታገልንላቸው መፈክሮች በመጮሃቸው ብቻ አብዮታዊና፥ የዚያን ጊዜ ሥርዓት አስደንጋጭ የነበሩ በመሆኑ በጥልቀት ይዘታቸውና አንደምታቸው ተበራይቶ አልወጣም ነበር:: ስለዚህም መፈክሮቹ ሊጣመሙ፤ ባዶአቸውን በቃል ብቻ ሊስተጋቡና በተዛባ መንገድ

በተግባር ሊውሉ በቁ:: መሬት ለአራሹና÷ መሬትን ማገር ተወራራሽ መስለው በመቅረባቸው የሕዝብን ሥልጣን የቀማው ደርግ÷ መሬትን አግሮ አርሶ አደሩን የራሱ ጢሰኛ አደረገው:: የመንግሥት ሥልጣን ጥያቄ ወሳኝና ቀዳሚ መሆኑን ያልተገነዘበው ሁሉ÷ አዋጁን መደገፍ ከሥራ መዋሉ ወይም ተግባራዊ ያደርግዋል ተብሎ ከሚጠበቀው ሥልጣን ጋር መያያዙ ግልፅ አልሆንለት አለ :: የአፄው ሥርዓት ኦኮኖሚያዊ መሠረት ቢመታም÷ አርሶ አደሩ ለነፃነት ሳይሆን ለኮታ ግበራና ለከፋ ጪሰኝነት ታጨ፤ተዳረገ :: ሕዝባዊ መንግሥት የተባለውንም በሕዝብ ስም ሥልጣን ይዞ ሕዝብን መግዛት ተደርጎ በገቢር ሲተረጎም÷ ለሕዝብ ቆመናል ያሉ ክፍሎች ሳይቀሩ ለመጀመሪያ ጊዜ ሰፊው ሕዝብ የራሱን መንግሥት አገኘ ብለው ለፈፉ፤ አሌ ባሉትም ላይ ከደርጉ ጋር አብረው ዘመተባቸው:: ወያኔ ሥልጣን ሲይዝም ምሁር ተብዬዎችና አንዳንድ የቅፅበታዊ ህልውና ባለቤት "ድርጅቶች" አርሶ አደሩ ገና ዛሬ የራሱን መንግሥት አገኘ እንዳሉን ዓይነት መሆኑ ነው:: የብሄረሰብ መብት የተባለውም ከመፅሐፉ--ከርዕዮቱ በተገኘው መልክ መብትን ማወቁ አንድነትን ያጠናክራል በሚል ቅን ዕምነትና ተስፋ ሙሉ መብት ሲታወቅ÷ አያያዙን አይተህ ጭብጦውን ቀማው ነውና በተገኘው ቀዳዳ የግድ የግንጠላን መፈክር አስተጋብተው ጠባብ ብሄርተኛነትን አቀነቀኑ:: ሶሻሊዝም ይምጣ ካላችሁማ ብለው አሿፌ መኮንኖች ግራ እጃችሁን አውጡ በሚለው ተወስነው ፋሺስታዊ አገዛዛቸውን አሰፈኑብን:: ወያኔ ደግሞ በብሄረሰብ መብት ሽፋን አንቀፅ 39ን እነሆ ያላቸው ጮቤ ሲረግጡ÷ የመብትን ጎልውና  ጭራሽ ደብዛ አጥፍቶ የራሱን የብቸኛ የበላይነትና ጨቋኝ አገዛዙን÷ ተጨቆኑ ባላቸውም ላይ ሳይቀር እንዳሰፈነው ነው::

ኢሕአፓ ከተመክሮ ማነስና ከትግሉ ፈጣን ሂደት ጋርም በእኩል- በትክክል ለመጓዝ ባለመቻሉ÷ ስህተቶችን የፈፀመ ቢሆንም÷ በጊዜ ደግሞ ለማረም÷ ለመታረም መጣሩ የሚታወቅ ነው:: ሳይውል ሳያድር ከወያኔና ሌሎችም ጋር በመሠረታዊው የዴሞክራሲ ጥያቄና የዚሁ አካል በሆነው በብሄረሰብ ጥያቄ ዙሪያ ግልፅ ልዩነቱን አውጥቶ ትግል አካሂዷል:: የብሄረሰብ ችግር በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ በአንድነት ጥላ መከበር አለበት ሲልም÷ ከእነወያኔ  ገና ከጠዋቱ ተለይቶ በመታገሉ ወያኔና ሻዕቢያም ዘምተውበታል:: የደርግ አገዛዝ ለሕዝብ እንደማይበጅም፤የመሬቱም አዋጅ ከፖለቲካ ሥልጣን ተለይቶ መታየት እንደሌለበት፤ በሕዝብ ላይ ራሱን ያስቀመጠ ኃይል ኢዴሞክራሲያዊ እንደሆነም  ዕምነቱና አቋሙን ይፋ አድርጎ የሕዝብን ቀጥተኛ ተሳትፎ የሚያረጋግጥ ከሁሉም የተውጣጣ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም ብሎ በመታገሉ የአረመኔ ሽብር ሰለባ ለመሆን በቃ:: ይህ ክቡር ደም የተከፈለበት ተመክሮም ከሁሉም በላይ ግልፅ አድርጎ ያስቀመጠው ከመነሻው- መድረሻው ይታወቃልን ሲሆን÷ ገና ከወዲሁ፤ ታጋይ ነኝ ያለው ኃይል ቤተመንግሥት ከመግባቱ በፊት፤ ትግልም  ራሱ ከመፋፋሙ አስቀድሞ ለምን እንደምንታገልና ዓላማችን ምን እንደሆነ መታወቅ፤ጥርት ብሎ መቅረብ እንዳለበት ነው::??? የሽፍንፍን መፈክሮች፤ ይዘታቸው ግልፅ ያልሆኑ ግቦች፤ ሰማይን ዝቅ አድርጌ አስጨብጣችኋለሁ ባይ ፕሮግራሞች ለአምባገነኖች መንድርደርያ ያመቹ መሆናቸውንም ተመክሯችን አሳይቶናል :: በዴሞክራሲ ስም ደግሞ ስንት ወንጀል እንደተፈፀመ ፤ ስንት ሕዝብ እንደተፈጀ የዓለም ሕዝብ ታሪክ በጠቅላላ ምስክር ነው:: ስለዚህም ራዕይ ሲሉ ራዕይ ስንል በሚል እንደተቸነው ሁሉ ዴሞክራሲ ሲሉ ዴሞክራሲ ስንል ብለን በተደጋጋሚ አቋማችንን ግልፅ ለማድረግና ከአስመሳዩም ለመለየት የምንጥረው ለዚህ ነው:: ኢሕአፓ የተመሰረተበትን 32ኛ ዓመት ስናከብር አቋማችንን እንደገና ግልፅ ማድረጉ ተገቢም ሆኖ አግኝተነዋል::

ብልህነት የጎደላቸው ጥራዝ ነጠቅ ገዢ ነን ባዮች÷ በእኛም ላይ የፈነጩብንና እየፈነጩብን ያሉ ቢሆኑም÷ በግልፅና በማያሻማ መንገድ የመጣነው ልንበዘብዛችሁ፤ መብታችሁን ልንቀማ፤ ሀገርን ልናወድም ነው ብለው እንዲናዘዙ አይጠበቅም:: ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር የለችም አልነበረችም ብሎ ግን "የለም" ያለውን ሊያጠፋ የሚራወጠው ወያኔም ቢሆን ትግራይ ተገንጥላ የራሷን መንግሥት ማቋቋም÷ ፍትሀዊና የግድ ነው የሚለው የአርዮስ አቋሙ ሲጠላበት÷ ሲተፋበትና ሲረክስበት÷ ዳቦ ሳይቆርስና ሳይቀደስ--

ሳይባረክ፤ በተለይም አጥፍቼ ነበር፤ ሀገርን ክጄ ነበር፤ ታሪክን አራክሼ ነበር ብሎ ስህተቱን ሳያምን፤ ንስሐ ሳይገባ፥ ራሱን የኢትዮጵያ ማለትም ኢሕአዴግ ብሎ ሰይሞ ዕመኑኝ--ተሞኙልኝ እንዳለም አይተናል፡፡ የታገልኩትና ዛሬም ሕዝብ ባይፈልገኝም ቤተ መንግሥት ያለሁት ለሕዝብ ስል ነው ብሎ ይለፍፋል እንጂ፥ ለግል ጥቅሜ፤ ስግብግበነቴን ላረካ፤ ሀገር ልዘርፍ ላጠፋ ነው ብሎ አይለፍፍም፡፡ ሕዝቦችን ሲጨቁን፥ የጭቁኖችን መብት በክልል ፊርጄ አስከብራለሁ ይላል እንጂ፥ ከፋፍዬ እርስ በእርስ ላጫርሰው ነኝ አይልም፡፡ መፅሐፍት ከማንበብ ይልቅ ከኢሳይያስ ጋር መወያየቱ ይበልጥብኛል ያለው መለስ፥ ዛሬም ባድሜና አዲ ኢሮብንም በከፊል አስረክቦ ባለበት ወቅት፥ ኢትዮጵያ ከሀያ በመቶ በላይ ተጨማሪ መሬት አግኝታለች ብሎ ይቀጥፋል፡፡ በአጭሩ፤ ሳንጠራቸው መጥተው በላያችን የሰፈሩብን ጭራቆች ሆኑ፥ እነዚህንም እያዳነቁ ያሉት ቅጥረኞች፥ መቸም ቢሆን መቅጠፋቸውንና በዴሞክራሲ ስምም መማል-መጀዘታቸውን አይተዉም፡፡ በወረቀት ደረጃ የሕዝብ መብት ይከበራል እያሉን፥ በገቢር ግን የተቃወመውን ሁሉ ወህኒና ጥይትን ቀለቡ የሚያደርጉትም ለዚሁ ነው፡፡

ጠላት ቢያባብሉት ወዳጅ አይሆንምና ጨቋኝ ገዢዎች ዴሞክራሲያዊ ሆነው እንዲገኙ አንጠብቅም፡፡ ሰለዚህም የሚጨንቀንና ይበልጥ የሚያሳስብን የእነሱ ሳይሆን፥ ወዳጅ ነኝ የሚለው ክፍል፤ ተቃዋሚ ነን የሚሉ አንዳንድ ክፍሎችና ነግ የሥልጣን ባለቤት እንሆናለን ብለው የሚያቋምጡ ጥቂት ቡድኖች ብቻ ናቸው፡፡ ነገ፥ "ወዳጄ ስለው በለጠኝ፤ ስለቴ ስለው ቆረጠኝ" እንዳይመጣ፥ ከወዲሁ በጉን የበግ ለምድ ከለበሰው ቀበሮ መለየቱ አስፈላጊ ነው፡፡ ዛሬ፤ ብዙዎች በዴሞክራሲ ስም ይምላሉ ፤ ይገዘታሉ፡፡ ከወቅቱ ጫጫታ ጋር የሄዱ መስሏቸውም ለአሜሪካው ዴሞክራሲ፤ ለአሜሪካው ካፒታሊዝም ቆመናል ባዮችም አሉ፡፡ ወያኔ ወድቆ እኛ ሥልጣን ከያዝን፥ ዴሞክራሲ በዴሞክራሲ አላብሰን እናሳልፍላችኋለን የሚሉንም በርካታ ናቸው፡፡ ይህን ሁሉና ሌላም ሌላም ቢሉም ግን፥ ጠጋ ብለን በሚያጎላ መነፅር፤ ቅንቅንን በሚያሳይ መብራት ስናያቸው ደግሞ፥ የለፈፉት ዴሞክራሲ አፋዊ ብቻ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በሕዝብ እኩልነት አያምኑም--ወይ ጠባብ ወይ ትምክህተኛ ሆነው ይገኛሉ፡፡ ከእኔ ኃይማኖት ሌላ ይውደም ባይም ሆነው ይጋለጣሉ፡፡ መብት እናስከብራለን ቢሉም የሠርቶ አደሩን ሕዝብ በጭፍን መበዝበዝ ደጋፊ ሆነው ይከሰታሉ፡፡ ሀገር ወዳድ ነን ቢሉም፥ ለባዕድ ሲጎነበሱና የባዕድ ሎሌ ሲሆኑ ይታያሉ፡፡ በአጭሩ፤ ቃላቸውና ግብራቸው፤ የሚሉትና የሚያምኑት የተለያዩና ተቃራኒ ሆኖ ይገኛል፡፡ እነዚህ ለሥልጣን ቢበቁ፥ ከወያኔ ያልተናናሰና በመሠረቱም ልዩ ያልሆነ አምባገነን ሥርዓት እንደሚጭኑብን ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ ጨቋኝን በሌላ ጨቋኝ መቀያየር ፍላጎቱ ያልሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዛሬው ጀምሮ ማን ዕውነትም ለመብቱ እንደሚቆምለት፤ ማን ደግሞ ውዳሴ ከንቱ እያሰማና ራሱን ሕዝባዊና ዴሞክራሲያዊ እያለ ዳግማዊ ደርግ፤ ዳግማዊ ወያኔ ሊሆን እንዳቆበቀበ መለየት መቻል አለበት፡፡ በድሮ ጊዜ ወዳጅ፥ ወዳጁን አይከዳም፤ ከጅብም በላይ ሆዳም የለም ይባል ነበር፡፡ ዘመን ተለውጦ ዛሬ ጅብን ጥመኛና ባሕታዊ የሚያስመስሉ ከርሰ - አዳሮች እንድ አሸን መፍላታቸውን እየታዝብን ነውና፥ ወዳጅ ነኝ ያለውን ሁሉ ፤ሕዝባዊ ነኝ ያለውን ሁሉ፥ በቃሉ መውሰድ--ማመን ሞኝነት ይሆንብናል፡፡ ያለፈው የትግል ታሪካችንን እኛንም ጨምሮ የሰጠን አንዱ ትምህርት ይህ ነው፡፡ እንዶድ በገርነቱ ውሃ ወሰደው የተባለው እንዳይደርስብን አበክረን እናሳስባለን፡፡

ይህንን ሁሉ ማለታችን፥ በአለብን ግዴታ ከወዲሁ አደራ ጠንቀቅ እንበል ለማለት ሲሆን፥ ከዚህ ባሻገር ግን በጣት ቅሰራው ለመሰማራት ፍላጎቱም ዓላመውም የለንም፡፡ የጠቁም--አጋልጥ ሰለባ ሆነን የደም ዋጋ መክፈላችንን ስለምናውቅ፥ የውንጀላ-ጥቆማ ስምሪት፥ የእኛ ተግባር ሊሆን አይችልም፡፡ በሌላ ገፅታው ደግሞ፥ ሀገር ስትጠፋ፥ ወይም ስትጎዳ እያየን-እየሰማን፥ "ዝም አይነቅዝም" ትክክል ስለማይሆን፥ ዕውነተኛ መስሎ ልብ የሚያቆስለውን፤ ኃሳዊ መሲሁን፤ በየካቲት 66 ይባል እንደነበረው አስመሳይ ተራማጁን፥

*ማጋለጡ-- ደካማ ዜጋ ነን ካላልን በስተቀር፥ የዜግነት ግዴታን ነው፡፡ ይህን ግዴታ ማማሏት ደግሞ የቃል ኪዳናችን አካል ነውና መሰሪና ቀበሮውን በስሙ መጥራት የግድ ይሆንብናል፡፡ ፋሽስቶች ሕዘባዊ ነን ሲሉ በጊዜ አጋልጠናል፤ ጠባቦች ኢትዮጵያዊ ነን ሲሉ ቀጣፊዎች ብለን ደባቸውን አሳውቀናል፤ የባዕድ ቅጥረኛውን ከሀዲ፤ ባንዳውን ባንዳ፤ ገንጣዩን ገንጣይም ብለናል፡፡ ይህንን ግዴታ ለማሟላት ደግሞ ዋጋ ከፍለንበታል፡፡ መንግሥቱ ኃይለማርያም ሽብር አውርዶብን ጀፍቶናል፤ ወያኔና ሻዕቢያ ከአንዴም ሁለቴ ሦስቴ ወግተውናል፤ ኢትዮጵያ ባልን የቅርብና የሩቅ ጠላቶች በደል ፈፅመውብናል፤ ከእነ ወያኔ አብረውም ጦር ልከውብናል፡፡ ግን ይህ ሁሉ አላንበረከከንም፡፡ ቃል ኪዳናችንን አልከዳንም፡፡ ኢትዮጵያዊ በክርናችን ለሥልጣን ፍርፋሬ አለወጥንም፡፡ ለሕዝባችን እኔ ልብላ አንተ ጦም እደር ብለን በመክዳት የራሳችንን ምቾት ፍለጋ አልሮጥንም፡፡ ቢሆን ኖሮ፥ ደርግም፤ ወያኔም፤ ባዕዳንም ሹመት-ሽልማት ባሉን ቁጥር ከጴጥሮስ በባሰ ፍጥነት፤ ዶሮም አንዴ ሳይጮህ ሀገርና-ሕዝብን በካድን ነበር፡፡ የ 32 ዓመት ታሪካችን ግን አረም አልፎ አልፎ ቢበቅልብንም፥ ኢሕአፓ እንደ ድርጅት በ1964 ዓ.ም ለሕዝብ የገባውን ቃል ኪዳን ፈፅሞ እንዳለፈረሰ ያረጋግጣል፡፡ ወደፊትም ታሪክና መጪው ትውልድ፥ ይመሰክረዋል፥ ያረጋግጠዋል፥ ይፈርደዋልም፡፡ ይህም ዕምነታችን፥ እስከዛሬ በትግል ፀንተን እንድንቀጥል አድርጎናል፥ ጠቅሞናልም!*

*ኢሕአፓ ሲመሠረት ጀምሮ የሀገርን ሉዓላዊነት፥ የሕዝብን መብትና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ዕውን በማድረግ አረጋግጣለሁ ብሎ የተነሳ ሲሆን፥ በትግሉ ሂደት ደግሞ ይህ ምን ማለት እንደሆነ በተገቢው መንገድ እንዲገነዘብ የግድ ሆኖበታል፡፡ ዴሞክራሲ ያለገደብ ለጭቁኑ ሕዝባችን ያለው ትክክለኛ መፈክሩ ዛሬም የፕሮግራሙ እምብርት ሆኖ የሚገኝ ሲሆን፥ ዴሞክራሲ የሚለው ቃል ግን የአምባገነኖችም አፍ መፍቻ ሆኖ በመምጣቱ ዴሞክራሲ ሲሉ ዴሞክራሲ ስንል ማለት የግድ ይሆንብናል፡፡ ለኢሕአፓ፥ ዴሞክራሲ የሚለው ቃል የሕዝብን ሙሉ በሙሉ--በፖለቲካውም፥ በኢኮኖሚውም፥ በማኅበረሰባዊውም-- የመብት ባለቤትነት የሚያረጋግጥ ነው፡፡ የተሸራረፈና የታቀበ መብት ሳይሆን፥ ሕዝብ በሕዝብነቱና በሀገር ባለቤትነቱ ባለሙሉ መብት የሚሆንበት ማለታችን ነው፡፡ በዘረኝነት የተቀየዱ ባዕዳን የአፍሪካና የሦስተኛ ዓለም ሕዝቦች፥ ምዕራባውያን ወይም ፈረንጆች ያላቸውን ሙሉ መብትና ዴሞክራሲ ሊኖረው አይጠበቅም ያሉትን የማንቀበለው ነው፡፡ በአንፃሩ ግን ከሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታና ባህል በተቃረነ ደረጃ ደግሞ የባዕድን ተመክሮ እንዳለ ገልብጦ ለማስፈን መጣሩ ፍሬ የሚኖረው አይሆንም፡፡ ኢትዮጵያውያን ኢትዮጵያውያን እንጂ አሜሪካዊ ወይም አውሮጳዊ አይደሉም፡፡ ከሌሎች ተመክሮና ልምድ ቀና ቀናውን መውሰድ ሲገባን፥ እሰስ ገሰሱን ሁሉ ማግበስበስ ደግሞ ራስን ለችግርና ቀውስ ማጋለጥ መሆኑ አይቀሬ ነው፡፡ እኛ በበለፀጉ ሀገሮች ደረጃ ባንገኝም፥ መብት አልባ ሆነን በአምባገነን ተቀጥቅጠን ለመገዛት የወሰነብን መለኮታዊ ፍርድ የለብንም፡፡ ስለዚህም ዴሞክራሲ ስንል መብታችንን ገድበው፥ ለዘብተኛ ፈላጭ ቆራጭ መች ይህ አነሳችሁ? የሚሉንን ልንቀበል አይጠበቅብንም፡፡ ለሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ቦታ እንስጥ ስንል፥ መብታችን ይገደብብን ለማለት ሳይሆን፥ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓታችን የራሳችንን ማኅተምና አሻራ መያዝ እንዳለበት ለማስገንዘብ ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ በደፈናው ነፃ ወይም ሊበራል ዴሞክራሲ የሚባለው፥ በገቢር ዴሞክራሲን ገድቦ እንደሚገለፅ የምናየው ነው፡፡ ለምሳሌ የፌዴራላዊ አወቃቀርን መረጥን ስላልን፥ የጀርመንን፤የስዊስን፤የናይጄሪያንና የአሜሪካንን ተመክሮ እንዳለ መገልበጥ አለብን ማለት አይደለም፡፡*

*"የምትለብሰው የላት የምትከናነበው አማራት" የሚሉን ባይጠፉም ለእኛ የዴሞክራሲ ወናው መከሰቻው፥ ሕዝብን የመምረጥና የመመረጥ መብት ባለቤት ማድረጉ ብቻ*

አይደለም። በእርግጥ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ምርጫ እያለ በሚያካሂደው እጅ እጅ ያለ ባልት አማካኝነት፥ ሕዝብ የምርጫ መብቱ ተከብሮለታል ብሎ ቢለፍፍም፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ ዛሬም ፖለቲካዊ መብቱን ተነፍጎ ከውሳኔ ጠርዝ ላይ በጠመንጃ ተገድቦ የነገ ዕጣውን ዳግም ሊነጥቁት ገዢ ተብዬውች ሲወራጩ ከማየት ያለፈ ሚና የለውም። ድርጅቶች በቦታው ተገኝተው መወዳደራቸው በራሱ የዴሞክራሲን መስፈን አመልካች ባይሆንም፥ በእኛ ተጨባጭ ሁኔታ ደግሞ ሕዝቡ የራሴና ይወክለኛል የሚላቸው ድርጅቶች ከውድድሩ ሂደት ተገልለው እንዳሉ እያየ ነው። በአጭሩ፥ ያጣን የነጣን ብንሆንም፥ ማግኘት ካለብን ደግሞ ከፍርፋሪ በላይ ዳቦውን ከእነእምቡጡ መመኘታችን ኃጢያት አይደለም። ምርጫ መካሄዱ ወይም መድብለ ፓርቲ ሥርዓት መረጋጋጡ ለራሱ በራሱ ብቻ ዴሞክራሲን አይገልጥም። ለእኛ፥የዴሞክራሲ መብቶች በትርጉሙም፥ በይዘቱም ሰፋ ያሉ ናቸው። በአንዳንድ ሀገሮች አንድ ወይም ሁለት ወይ የተወሰኑ ድርጅቶች እርስ በርሳቸው እየተወዳደሩና ሥልጣን እየተቀያየሩ በሕዝብ ስም ሕዝብን የሚገዙበትን ሁኔታ ዴሞክራሲ ብለን ልንመኝ አንፈልግም። በቀድሚያ መታወቅ ያለበት መሠረታዊ ሀቅ ቢኖር፥ ማንም ቢሆን ማን ከሕዝብ መሠረታዊ መብቶች ውስጥ፥ በሰላሙ ሁኔታ መቀነስ ወይም መገደብ ከቶም እንደማይችል ነው። መብት የድህነትና የብልፅግና ጉዳይ ሳይሆን፥ የሰውነት ጉዳይ፤ ሰብዕናን የማረጋገጥ ጥያቄ ነው። ድሆች ነንና ፥ ከሁለት ወይም ሦስት ፓርቲዎች/ድርጅቶች በላይ ሊኖሩን አያስፈልግም ብሎ ይህንኑ ለመደንገግ መነሳት፥ የሕዝብን መብት ከመገደብ ሌላ ትርጉም ሊሰጠው አይቻልም። ሥልጣንን ለሕዝብ ሳይሆን ለተወሰኑ ድርጅቶችና እነዚህም ለሚወክሉት ምርጥ ክፍል ለማረጋገጥ ነው የሚሆነው።

ዴሞክራሲ ስንል፥ ዕድገትን ለኅብረተሰቡ ሊያረጋግጥ በሚችል መልኩ ሲመጣ ብቻ ነው ማለታችን ነው ። ከድርጅቶች በነፃ መንቀሳቀስና፥ ነፃና ፍትሐዊ ምርጫም ከመረጋገጡ ባሻገር፥ ሕዝብ በቀጥታና በራሱ ነፃ ማኅበራትና ተቋማት አማካኝነት የሥልጣንና የውሳኔ አካል የሚሆንበትን እውን ማደረግ ነው። ተመክሮ እንዳሳየን፥ የሥልጣን ጥም፥ ከፖለቲካ ቀለምና ርዕዮት የተነጠለ ክስተት ነው ማለት ማጋነን አይሆንምና ወይም ሥልጣን የማያበላሸው ብዙ ባለመሆኑ፥ ሕዝብ መረጥኩህ ያለው ኃይል በሥልጣን ባልጎ እንዳያስቸግርም ማገጃ መከላከያ ያሻዋል። የመረጠውንም የማውረድና የማስወገድ መብት መረጋገጥ አለበት ማለት ነው። ሕዝብ ወኪሎችህ ነን ለሚሉት ድጋፍ መስጠቱ ብቻ ሳይሆን፥ ዋናው ቁም ነገር ራሱ በህግ ውሳኔና፥ በወሳኝ የሀገሩ ጉዳዮች ላይ መወሰን መቻሉ ነው። ስለዚህ ዴሞክራሲ ስንል፥ ሥልጣን በመንግሥት ተብዬው ብቸኛ ቁጥጥር ስር ሳትሆን ፥ ሕዝብ በራስ አስተዳደር ደረጃ ባለሥልጣን የሚሆንበትን ሥርዓት ማረጋገጥ ነው። ይህም ፓርላማ በሚባለውም ደረጃ የሕዝብ የራሱ ተሳትፎ በሕዝባዊ ድርጅቶቹም አማካኝነት የሚገለፅበትን መንገድ መሻት የግድ ይላል። ዴሞክራሲ ስንል አንዳንዴ ይዘታቸው ግልፅ ባልሆነ የግል መብቶች ላይ በማተኮር ሕዝብን በይስሙላ ዴሞክራሲ የበይ ተመልካች ማድረግ ሳይሆን፥ የጋራ ዕድገትና ብልፅግናን ቅድሚያ በመስጠት ማኅበረሰባዊ ተሳትፎን የሚያረጋግጥ ሥርዓትን ማስፈን ማለታችን ነው። የሕዝብን ቀጥተኛ ተሳትፎ፤ የሕዝብን የጤናና የትምህርት ሁኔታ ቅድሚያ የሚሰጥ፤ የኅብረተሰቡንና የሀገሪቷን ደህንነት የሚያስቀድም- የሚያረጋግጥ መሆን አለበት። ዴሞክራሲ ሰፍኗል ተብሎ ጥቂቶች ብዙሀኑን ያለመረንና ገደብ እየበዘበዙ የሚንደላቀቁበት ሥርዓት ማለታችን አይደለም። ዴሞክራሲ የሕዝብን መብት በኤኮኖሚውም መስክ መረጋገጡን የግድ ይላል። ብዙኃኑ ከድህነት የመላቀቅ መብት አለው የሚለውን ያረጋግጣል። በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ህፃናት መንገድ/ ጦም አዳሪ፥ የምርጦቹ ልጆች ደግሞ ተንደላቅቀው በሳንፎርድና በኬምብርጅ- በባዕዳን ትምህርት ቤቶች ጠግቦ አዳሪዎች የሚሆኑበት ሥርዓት ሊሆን አይችልም። ጥቂቶች በቦሌ ቪላዎች፤ሚሊዮኖች ደግሞ በድልድይ ስር ራቁታቸውን የሚያድሩበት ሥርዓት ሊሆን አይችልም። ሕዝብ፥ ፖሊስና ወታደሮችን፤ ባለስልጣንና መንግሥት የሚባሉትን እየፈራ፤ እየባነነ የሚኖርበትን ሳይሆን፥ ገዢዎች ነን የሚሉት፥ የሥልጣን ባለቤቱን ሕዝብን እራሱን የሚፈሩበት ሁኔታ ነው ዴሞክራሲን የሚገልጠው። የሥልጣን ማዕከል ሕዝብ ሆኖ፥ በገቢር ሲከሰት ወይም ሕዝብ በፖለቲካ ፖሊሲዎች ወይም እርምጃዎች ዋና ወሳኝ ሆኖ ሲገኝ፥ ስለ

ዴሞክራሲ መስፈን አፍን ሞልቶ መናገር ይቻላል፡፡ ዲሞክራሲ ስንል ምልዓተ ሕዝብን አሳታፊ ዲሞክራሲ ማለታችን ነው፡፡

በሕዝብ ስም የሚናገሩ፤ ፀሐይና ጨረቃ ለጭቁኑ ሕዝብ በእጃችን አለ የሚሉና፥ ለሥልጣን ሲበቁ ደግሞ፥ ከመቅፅበት በሕዝብ ላይ ቀንበር ጫኚ የሚሆኑ ጥቂቶች አይደሉም፡፡ ዴሞክራሲንም ባፈተታቸው ተርጉመወና በዋና መልኩ ደግሞ በአፋዊ ደረጃ ገድበው፥ የሚገዙም በተለይ በአፍሪካ ብዙዎች ናቸው፡፡ በራሳችን ሀገር ደግሞ ለሰፊው ሕዝብ ቆሜያለሁ ብሎ፥ በሰፊው ሕዝብ አስከሬን ላይ ዳንኪራ የረገጠውን ደርግ፤ የሕዝብን ትግል ቦታ ሳይሰጥ፥ በራሴ ትግል ለድል በቃሁ ባዩና ከሕዝባዊም አልፎ የነቃሁ የበቃሁ በአልባኒያ ቲራና የምስክር ወረቀት የተሰጠኝ ኮሙኒስት ነኝ ይል የነበረው ወያኔ፥ ዴሞክራሲያዊ ነን ብለው በሚመፃደቁ ባዕዳን ድጋፍ ለሥልጣን ሲበቃ ፥የነቃ የከፋ ዘረኛና ፀረ ኢትዮጵያ ሆኖ፥ እነሆ አስራ ሦስት ዓመት አስቆጥሯል፡፡ መብታቸውን አውቄላቸው ከጭቆና ነፃ አወጣኋቸው፤ ክልል ብዬ አቋቁሜ ራሳቸውን አስተዳደሪ አደረግኳቸው፤ የራሴን የምርጫ ህግና ቦርድ እውን አድርጌ እነሆ ነፃ ምርጫ መብት አልኳቸው ባዩን የመለስ አገዛዝ ተሸክመን አለን፡፡ ባዕዳን ዴሞክራሲያዊ ነው የሚሉት የመለስ አገዛዝ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሰይጣን የላከው መርገም ነው፡፡ መጣሁልህ የተባለው አርሶ አደርም ማንም ሳይጠይቀውና ሳያማክረው የመሬቱ እንኳን ባለቤት የመሆን መብቱን ተነጥቆ ለከፋ ብዝበዛ ተዳርጓል፡፡ በትግል በተገኘ ውሱን ድል፥ ኅልውናቸው ዕውን በሆኑት ነፃ ጋዜጦችና ጋዜጦች ላይ፥ ዴሞክራሲያዊ በተባለውና ሳንሱርን አስወግጃለሁ በሚለው የመለስ አገዛዝ እየደረሰበት/እየደረሰባቸው ያለውን መከራና እቀባ አይተናል፡፡ ዴሞክራሲ ስንል፥ ከልፈፋው ባሻገር በሀቅ እውን የሆነውን መመርመር አለብን፡፡ ዴሞክራሲ ስንል፥ በቅድሚያ ለጥቂቶች፤ ለምርጦች፤ ታድለናል ስንወለድም ተመርጠናል፤ በልፅገናል፤ተምረናል ለሚሉት ሳይሆን፥ ለሰፊው ሕዝብ ነው፡፡ ዴሞክራሲ በመሠረቱ ብዙኃኑን ይመለከታል፡፡ ብዙኃኑ የሲቪልና የፖለቲካ መብታቸው ባለቤት መሆናቸውን በቅድሚያ ይመለከታል፡፡ ከዚህ ሌላ ደግሞ "ብዙኃን ይመውዑ"-- ወሳኞች ብዙኃኑ ናቸው፥ ቢባልም የውሁዳን ወይም ህዳጣን መብትም፥ መከበሩ ዴሞክራሲ መኖር አለመኖሩን መለኪያ ነው፡፡ የብሄረሰብ፤ የኃይማኖትና የፆታ ልዩነትን አስፍቶና እኩልነትን ክዶ ዴሞክራሲ ሰፍኗል ማለት ዘበት ነው፡፡

የገዢዎቻችን ዴሞክራሲ፥ የዱባ ሰንጋ መሆኑን ደግመን ደጋግመን ያየነውና ቢያንስ የማይበጀን--የማንፈልገው እንደሆነ አውቀናል ማለት እንችላለን፡፡ ለገሰ አስፋው ሲሄድ ለገሰ ዜናዊ መጥቷል--ከሄደውም የመጣው ብሷል፡፡ አስመሳዮችና ኃሳዊ መሲሆች፤ አታላይ ዴሞክራቶች እንደ አሸን ይፈላሉ፤ ግን አትመኗቸው የተባለውም ዛሬ ሊደመጥ የሚገባው ነው፡፡ ድርጅቶች ስለራሳቸው ከሚያሰሙት ውዳሴ ሳይሆን ከተጨባጭ ይዘታቸው፤ ከሥራቸው፥ ከግብራቸው መገምገም አለባቸው፡፡ የሚያበሉ ሳይሆን የሚገርፉ ሊሆኑ ይችላሉና ሁሉም--ኢሕአፓም ጭምር-- በሥራው፥ በመግባሩ፥ በራዕዩ፥ በታሪኩ መገምገም ይኖርበታል፡፡ ዋናው ቁም ነገር ግን፥ የራስን መብት ወካይ ለተባለም ድርጅት ወይ ኃይል አሳልፎ መስጠት እንደማይገባ መረዳቱና ሥልጣን ያበላሻልና በራሳችን ላይ እባቡን ጠምጥመን፥ ለመከራና ሞት ራሳችንን እንዳናመቻች መጠንቀቁ ላይ ነው፡፡ ላለፈው አይፀፀቱም፤ ለሚመጣው አይበለጡም ማለት መቻል አለብን፡፡ በአፍሪካ እንዳየነው የራሳችን ታሪክና ባህል አለን በሚል ሽፋን፥ ዴሞክራሲን እንደ ባዕድ በመቁጠርና፥ ተቃውሞ ራሱ አፍሪካዊ አይደለም ብሎ በመደምደም አምባገነናዊ ሥርዓታቸውን ያሰፈኑ ጥቂቶች አልነበሩም፡፡ ከታሪካችንና ባህላችን፥ ራስን በሥርዓት ከማስተዳደር አንፃር ጠቃሚ ትምህርት ልናገኝ ብንችልም፥ የቀድሞውና የዛሬው ተጨባጭ ሁኔታ የተለየያ ነውና የትላንቱ እንዳለ ለዛሬ ይሠራል ብሎ መደምደም ስህተት ነው፡፡ በባኅል ስምም አስከፊና ጨቋኝ ልምዶችን በዘመናችን ለማስቀጠል መከጀሉ ሊደገፍ አይገባውም፡፡ ባዕዳን፥ "ይትም ፍጪው ዱቄቱን አምጪው" በሚል ጥቅማቸውን ለመጠበቅ አምባገነኖችንም እንደሚደግፉ ወይም ድህነትን ለመቀነስ በሚል፥ በጫና የሚገፉት ኢኮኖሚያዊ መዋቅር መሻሻል ወይም ለውጥ ለሕዝብ እንደማይበጅ በሠርቶ አደሩ ሕዝብ እንባ ታጅቦ የተረጋገጠ ሀቅ ነው፡፡

ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ሳይሰፍኑ የኤኮኖሚ ዕድገትን ጥያቄ ለሕዝብ በሚየረካ መንገድ መመለስ አይቻልም። ስታሊን በሶቭየት ኅብረት፣ ቹንግ ሂ ፓርክ በኮሪያ፣ ሊ ክዋን ዪው በሲንጋፖር አምበገናናዊ ሥርዓት አስፍነውና ሠራተኛውን ሕዝብ አፍነው ይዘው የኢኮኖሚውን ዕድገት አረጋግጠዋል ተብሏል። ይህ ዕድገት ተብዬ ግን ለጥቂቶች እንጂ ለብዙኃኑ የመጣ ካለመሆኑ ሌላ፥ የየሀገሩ ሁኔታ ደግሞ ከኢትዮጵያ ተመሳሳይ አይደለም። ዛሬ መለስ ዜናዊና ጭፍሮቹ የሀገሪቱ ዋና ችግር ድህነትና ኋላቀርነት ነው የሚሉን ኢኮኖሚና ዕድገትን ከዋናው የፖለቲካ መሠረት ነጥለው ትኩረታችን ሥርዓቱን ለመቀየር ሳይሆን፥ በመለስ መሪነት ድህነትን ለማጥፋት በተባለው ፍሬ ቢስ ስምሪት ላይ እንዲሆን ነው። "አህያውን ትቶ ዳውላውን ቀጥቅጥ ባዩ" ይህ አቋዋም የዴሞክራሲያው ሥርዓት መስፈን ቀዳሚና ወሳኝ ጉዳይ መሆኑን እንድንስት የሚቃኝ ነው።

ዛሬም ተቀዳሚ ተልዕኮአችን ጨቋኙንና ሀገር አጥፊውን የመለስን አገዛዝ አስወግዶ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ማስፈን ነው። ይህም ሥርዓት ህዝባዊ መሠረት ያለው፣ ኅብረተሰባዊ ተሳትፎን ያስቀደመ ፣ ሕዝብን ያገለለ ሳይሆን ያቀፈ ፣ የተገለሉትን ክፍሎች የሚያቀርብ፣ የተጨቆኑትን የመብት ባለቤት የሚያደርግ፣ የሕዝብን ደህንነት፣ዕድገትና ብልፅግና ከባድ ሚዛን የሰጠ መሆን አለበት። መለስን በሌላ አፈ ምላጭ አምባገነን ለመተካት ሳይሆን፥ ግፈኛውን ሥርዓት፥ የእኛ በምንለውና ከጠላነውም በምንለውጠው፥ ለጥቂቶች ሳይሆን፥ ለሁላችንም በሚበጀን ለመተካት መሆን አለበት። የአረመኔ ልቡ ቀጋ መሆኑን ያየንና እያየንም ያለን ነንና ከእንግዲህ የመለስ አገዛዝ ሊያደናግረን የሚችል አይደለም። ተብስን አውቀናታል፣ ትሻል ነኝ ባይዋን ግን ከቅርብ መመርመር ግዴታችን ነው። ዳግም የትግላችንን ውጤት እንዳንቀማ፣እንደገና በአፈ ጮሌዎች እንዳንሞኝ፣ የመብታችን ባለቤት ራሳችን መሆናችንን ለማረጋገጥ፣ የመብታችንን ሞግዚት ከቶም ላለመቀበል፣ "በእጅ አግብቶ ቁንጣን" ከተባለው ለመዳን አስተውለን መገንዘብ ይኖርብናል።

ታሪኩ በግልፅ፥ እንደሚያሳየው፥ ኢሕአፓ ለሕዝብ የሚበጅና የሕዝብን ሀቀኛ ሉዓላዊነት የሚያረጋግጥ ሥርዓት እስኪመሠረት ድረስ፥ ግንባሬን አላጥፍም፣ ትግሌን አላቆምም ብሎ ለሕዝብ በገባው ቃል ኪዳን መሠረት፥ ከሕዝብ ጎን ቆሞ እየተዋደቀ ነው። ሰላሣ ሁለት ዓመት ሆነን ስንልም፥ ይህንን ፅናትና ቃልኪዳን ለማደስ፣ሰማዕታትን ለመዘከር፣ ለሕዝብ ለሚጠቅም ዴሞክራሲ ትግላችን ይቀጥላል ለማለት ነው።

መጋቢት 24/ 1964 የኢሕአፓ መሥራች ጉባዔ ተጀምሮ በሚያዝያ 1 ተደመደመ። ጊዜ መምህር ነውና ከዚያ እስከዚህ ብዙ ተምሯል፣ በትግሉ ሂደትም ሊያመልጣቸው ካልቻላቸውን ስህተቶች ተመክሮ ቀስሟል፣ ፅንቶ በቆራጥነት በመታገል ደግሞ አዲስ ትውልድ ሞት አይፈሬና ታሪክና ሀገርን አስከባሪ መሆኑን አስመስክሯል። ገበሬ የሚያጭደው የዘራውን ስንዴ ብቻ አይደለምና ኢሕአፓም ከጉያው ወጥተውና ቃል ኪዳናቸውን ሽረው ለጠላት ያደሩና የጎዱትንም (ዛሬም ለወያኔ ያደሩትንም) በተመለከተ ሆነ ፣ የሕዝብን ፍላጎት ማስቀደምን በተመለከተ፣አውቅልሀለሁ ብሎ በማሰብም ሆነ ባለማሰብ የሕዝብን ቦታ መውሰድን በተመለከተ፣ ወዘተ የማይናቅ ግንዛቤን አግኝቷል። ኢሕአፓ ሲታገል በስህተት ለፈፀማቸውና ለደረሰበት ጉዳት ጉዳዩን በጥሞና መርምሮ ግለ ሂሰ ቢያደርግም፥ በቆራጥነት በመታገሉ ግን ይኮራል አንጂ አይሸማቀቅም። በስልት መታገልና ተገቢ ዘዴን በሥራ ማዋል ጠቃሚነቱን ቢቀበልም፥ ለዚያድ ባሬም፣ ለሻዕቢያም፣ ለባዕዳኑም ሁሉ አድሮ ተነጥፎ ወደ ቤተመንግሥት ባለማምራቱ፥ ቁጭት ሳይሆን፥ ያለው ስሜት ኩራት ነው። ኢሕአፓ ሕዝባዊ ዓላማውን ለሥልጣን ሸጦ፥ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የባዕድ ተጠሪ፣ ዳግማዊ ደርግ-ወያኔ ከሚሆንና የሕዝብን መከራ ከሚያባብስ ቢቀር ይሻላል ባዩ ኢሕአፓ ራሱ መሆኑ ደግሞ፥ የታየና የተረጋገጠ ነው። ኢትዮጵያ ሀገራችን ዛሬ ከመቸም ጊዜ በበለጠና በከፋ አደጋ ላይ ሆና ባለችበት ወቅት፥ ለአዬውም ሆነ ለደርጉ ሥርዓት እጅ ያልሰጠው ኢሕአፓ ሰላሣ ሁለት ዓመት በሌላ ሰላሣ ሁለት ዓመት ቢደገም፥ ለፀረ ሕዝቡ የመለስ አገዛዝ ሊነበረከክ ጭራሽ የሚጠበቅም የሚታሰብም አይሆንም።

**ከሚያዝያ** 1964 **እስከ ሚያዝያ** 1996 **ብዙ ዓማታት አልፈዋል፤ ብዙ ሁኔታዎች ተለውጧልም፡፡ የኢሕአፓ ሕዝባዊነትና ፅናት ግን የሰናፍጭ ቅንጣት ታህልም ለወጥ አልደረሰበትም፡፡ ይህንንም ሀቅ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሚገባ ያውቅለታል፡፡**

**ትግላችን ይቀጥላል**!!
**የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝብ ያችንፋል**!!